# የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች (Divided Society) እና የሕገ-መንግስት ንድፍ፤ ኢትዮጵያ በተከተለችው አማራጭ ላይ ምልከታ

*ጎሳዬ አየለ* *


## አህጽሮ-ፅሁፍ

*የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች የሚያጋጥማቸው አብይ ችግር በማንነት ላይ የተመሰረተ አለመግባባት ወይም ግጭት ነው፡፡ ይህ በቋንቋ ፣ብሄር፣ ኃይማኖት ወዘተ ልዩነት ላይ ተመስርቶ የሚነሳ አለመግባባት ወይም ግጭት ያለባቸው ማህበረሰቦች የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ይባላሉ፡፡ ለነዚህ ማህበረሰቦች በማንነት ላይ ተመስርቶ ለሚነሳው ግጭት ማረቂያ /management/ እንዲሆኑ ከቀረቡት መፍትሄዎች ወስጥ የሕገ-መንግስት ንድፉ ይህን ችግር እንዲቀርፍ አድርጎ መቅረፅ አንደኛው ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ  በጣም የሚታወቁትና ተወዳዳሪ ንድፍ ያቀረቡት አረንድ ላይፓርትና ሮናልድ ሆሮዊትዝ ናቸው፡፡ ላይፓርት የስምምነት ወይም የአስፈፃሚውን ስልጣን ማጋራት ሕገመንግስታዊ ንድፍ /Consociationalism/ ሲያቀነቅን ሆሮዊትዝ በበኩሉ የማሳሳብ ንድፍን /Centripetalism/ ይደግፋል፡፡ ሁለቱም ፀሀፊዎች የብዙሃን ዴሞክራሲ ንድፍ /Westminster majoritarian democracy/ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች የማይሰራና እንዳይተገብሩት ቢመክሩም አማራጭ ብለው ያቀረቧቸው ንድፎች ደግሞ በጣም የተለያዩ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግስት በማንነት ላይ ተመርኩዞ ሊሚነሳ አለመግባበት ወይም ግጭት መፍትሄ አንዲሆን ተብሎ የተቀረፀ ቢሆንም አነዚህ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች መፍትሄ ይሆናሉ ተብለው ከቀረቡት አማራጭ ንድፎች አንፃር ሲታይ  አነዚህ ንድፎችን በተገቢው መጠንና ዓይነት በአጥጋቢ ሁኔታ አላካተተም፡፡ ሕገመንግስቱን የቀረፁት ሰዎች የማሳሳብ ንድፍ ከናካቴው ከግምት ውስጥ አላስገቡም፡፡ የተወሰኑ የስምምነት ወይም የአስፈፃሚውን ስልጣን ማጋራት የሚጠይቀውን ንድፍ አንዳንድ ጉዳዮችን ያካተተ ቢሆንም ዋና ዋና የንድፉ መገለጫዎች የሆኑትን አንደ አስፈፃሚውን ሥልጣን ማጋራት እና ተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት የሚመለከቱትን አላካተተም፡፡ በተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ሰላም ማምጣት የሚቻለው ወይም በማንነት ልዩነት ላይ ተመርኩዞ ሊሚነሳ ግጭት ማረቅ የሚቻለው ሁለቱ ፀሃፊዎች እንዳቀረቡት አማራጭ ንድፎች ከሆነ የኢትዮጵያ ሕገመንግሰት ይህን ችግር የሚያስታምም ወይም የሚቀርፍ ንድፍ የለውም፡፡*


**ቁልፍ ቃላት፡-** የተከፋፈለ ማህበረሰብ ፣የስምምነት/ሥልጣን ማጋራት/ ዴሞክራሲ ፣የማሳሳብ ዴሞክራሲ

## 1. መግቢያ

አብዛኛው በአለም ላይ ያሉ አገራት ብዝሃነት መገለጫቸው ነው፡፡ በብሔር፣ በቋንቋ፣ በባሕል፣ በሐይማኖት ወዘተ ልዩነት የሌለበት ማሕበረሰብ ያለው አገር ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ብዝሃነት ባለባቸው የተወሰኑ አገራት አብይ የሆነ የሚያጋጥማቸው ችግር በተለይ በብሄር/ቋንቋ ልዮነት ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ ግጭት ነው፡፡ ይህ የብሔር/ቋንቋ ማንነት ላይ መሰረት ያደረገ አለመግባባት ወይም ግጭት ወደ ፖለቲካ ግጭት ሊያመራ ወይም ሊለወጥ

---

* ጎሳዬ አየለ፣ በሃዋሳ የኒቨርሲት ፣ ሕግ ትምህርት ቤት የሕግ መምህር:: ፀሃፊውን በሚከተለው የኢሜይል አድራሻ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ gosayeayele@gmail.com

ይችላል፡፡ በብሔር/ቋንቋ ልዩነት ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ችግር የሆነባቸው አገራት የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች (divided society) ተብለው ይጠራሉ[1]፡፡ ይሁንና ብዝሃነት በተለይም የብሔር/ቋንቋ ልዩነት በራሱና ሁልጊዜም የአለመረጋጋት ወይም የግጭት መንስኤ አይደለም፡፡ በመሆኑም ብዝሃነት መኖሩ በራሱ የማንነት ፖለቲካዊ ግጭት ሁሌም የሚያስከትል ባለመሆኑ ብዝሃነት ያለባቸው አገሮች ሁሉ የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ናቸው ማለት አይደለም፡፡

የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ያለበት አገር በብሄር/ ቋንቋ ልዩነት ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ቸል ሊባል የሚገባ ወይም የሚቻል ችግር አይደለም፡፡ ለዚህ ችግር ከሚሰጡ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ውስጥ ተቋማዊው መንገድ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ይህ የዴሞክራሲውና የሕገ-መንግስቱን ቅርጽ ይዘትና ንድፍን ይመለከታል[2]፡፡

በብሔር/ ቋንቋ ልዩነት ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ችግር የሆነባቸው አገራትን ምን ዓይነት የዴሞክራሲና ሕገ-መንግስት ንድፍ ሊያረግበው ወይም ሊቀንሰው ይችላል? የሚለው ላይ በንድፈ-ሐሣብ ደረጃ የዘርፉ ምሁራንን የሚያስማማ አንድ ወጥ የሆነ ንድፍ የለም፡፡ ምሁራኑ የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ያሏቸው አገራት ያለባቸውን በብሔር/ ቋንቋ ልዩነት ላይ የተመረኮዘ ችግር ለማስታመምና ለመምራት ያስችላሉ የሚሏቸውን የተለያዩ የፖለቲካ ተቋማዊ አደረጃጀቶች ያቀረቡ ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ ጐልተው የወጡት ግልጽ፣ ተነፃፃሪ ወይም ተወዳዳሪ ንድፎች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው የስምምነት/ስልጣን የማጋራት/ዴሞክራሲ (Consociational Democracy) ሲሆን ሁለተኛው የማሳሳብ ዴሞክራሲ (Centripetalism) ናቸው[3]፡፡

---

[1] Choudhry Sujit, Bridging Comparative Politics and Comparative Constiutional Law: Constiutional Design in Divided Soicieties: Integration or Accomodation. Oxford University Press, 2009፣ p. 4.

[2] ልዮነት (diversity or plural societies) ባለባቸው ወይም ብዙሃነት ባለባቸው አገራት በዚህ ላይ ተመርኩዞ ወይም በተያያዘ ለሚነሱ ግጭቶች ማስታረቂያ ወይም ማለዘቢያ ሶስት አጠቃላይ አቅጣጫዎች አሉ፡፡ እነዚህም ማመሳሰል (Assimilation)፣ ማዋሃድ (Integration) እና ማቻቻቻል (Accomodation) ናቸው፡፡ ማመሳስል (Assimilation) ልዩነትን የማይቀበል ብቻ ሳይሆን ልዩነቶችን ማጥፋት እንደአቀጣጫ የሚከተል ነው፡፡ ማዋሃድ (Integration) ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ባህላቸውን፣ ልማዳቸውን፣ ቋንቋቸውን ወይም ማንነታቸውን ማክበራቸው፣ መግለጻቸውን ባይከለክልም እንደማመሳሰልም (Assimilati on) ልዩነቶች መደፍጠጥ አለባቸው የሚለውን ባይቀበልም እንደማቻቻል አቅጣጭ (Accomodation) የመንግስት ወይም ይፋዊ ዕውቅና እንዲኖረው ግን አይፈቅድም፡፡

የማቻቻል ስትራቴጂ (Accomodation) በበኩሉ ማመሳሰልም (Assimilation) ሆነ ማዋሃድን (Integration) በጽኑ የሚቃውምና ልዩነቶች በግል ብቻ ሳይሆን ይፋዊ (Public) ዕውቅና ሊሰጣቸው ይገባል ብሎ የሚያምን ነው፡፡ ይህ ጥናት ከነዚህ አቅጣቻዎች ውስጥ የትኛው ነው ትክክለኛ ወይም በኢትዮጵያ ሁኔታ የትኛው ነው የሚያስኬደው? የሚለውን አይዳስስም፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሰት ቀራጮች የማመሳሰልም (Assimilation) ሆነ የማዋሃድ (Integration) ፖሊሲ በኢትየጵያ ሁኔታ የማይሰራ ነው በማለት አልተቀበሏቸውም፡፡ ለአገሪቱ ብቸኛው ሰላምን የሚያሰፍነው የማቻቻል ፖሊሲ (Accomodation) ነው ብለው ይህንን በሕገመንግስቱ አካተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብም የተከፋፈለ ማሕበረሰብ ነው አይደለም የሚለውን ጉዳይ ጥናቱ አይሞግትም፡፡ ጥናቱ የሚመለከተው የሕገመንግስቱ ቀራጮች በኢትዮጵያ በማንነት ላይ የተመረኮዘ ፖለቲካዊ ችግር የሆነና በማቻቻል ስትራቴጂ መፍትሄ ሊበጅለት ይገባል ብለው በማመን የቀረጹት ሕገመንግስት ንድፍ ለተባለው ችግር መፈትሄነት በቂነትና ተገቢነት ላይ ነው፡፡

[3] እንዚህን ጽንሰሃሳቦች ቀጥተኛ የሆነ ሁሉንም የሚያግባባ ቃል ስላላገኘሁ ተቀራራቢና ይገልጻቸዋል ብዬ ያስብኩትን ቃላት ተጠቅሚያለሁኝ፡፡ የበለጠ ለመረዳት እንዲረዳ የእንግሊዘኛውን ቃል ከጎኑ ሰፍሯል፡፡ ጽንሰሃሳቦች ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም ስለሌላቸው የማሳሳብ (Centripetalism) እና የስምምነት/የስልጣን ማጋራት (Consociationalism) ዴሞክራሲ ንድፍ ዋና መገለጫቸው በሚመለከተው የጥናቱ ክፍል በሰፊው ተተንትኗል፡፡

የዚህ ጥናት ዓላማ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ) ሕገ-መንግሥትን ከነዚህ ንድፎች (ሞዴሎች) አንፃር መገምገም ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት የማሳሳብ ዴሞክራሲ ሞዴልን (Centriptalism) አልተቀበለም፡፡ የስምምነት/የስልጣን ማጋራት/ዴሞክራሲ ንድፍን (Consociational Democracy) የሚያሳዩ ወይም የሚያመላክቱ ነገሮች የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ቢኖረውም ንድፉ የሚያዘውን አንኳር አንኳር መገለጫዎች ትቷቸዋል፤ ወይም አያካትትም፡፡

ሁለቱም ንድፎች እንደሚያስቀምጡት በብሔር/ቋንቋ ማንነት ላይ ተመርኩዞ ለሚነሳ አለመረጋጋት ወይም ግጭትን ለማቻቻልና ለመምራት ሁነኛና ብቸኛ መንገዶች ከሆኑ[4] ይህ ጥናት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ቅርጽና ይዘት በኢትዮጵያ ያለውን የብሔር ግጭት በዘላቂነት የሚፈታ የዴሞክራሲ ንድፍ የለውም ብሎ ይከራከራል፡፡

የመጀመርያው የጥናቱ ክፍል ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች አማራጭ ሆነው የቀረቡትን የማሳሳብ ዴሞክራሲና የስምምነት/ስልጣን የማጋራት/ዴሞክራሲ ንድፎች ይተነትናል፡፡ ከዚያም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት በብሔር/ቋንቋ ላይ ተመርኩዞ ለሚነሳ ፖለቲካዊ ግጭት ለማቻቻልና ለመምራት ያስቀመጠውን ንድፍ ይዳስሳል፡፡ በመጨረሻው ክፍል የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ሊኖራቸው ይገባል ከተባሉት የዴሞክራሲ/ሕገመንግስት ንድፎች አንፃር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግሥትን ይመረምራል፣ ይገመግማል፡፡

## 2. ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ተገቢ የሆነው የዴሞክራሲና ሕገ-መንግሥት ንድፍ፤ ንድፈ-ሃሣባዊ ዕይታ

በዓለም ላይ ያሉ አገራት ከብሔር፣ ከቋንቋ፣ ከባህል፣ ከሀይማኖት ወዘተ ልዩነት ጋር የተያያዘ ብዝሃነት አለባቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ልዩነቶች ሁሌም ፖለቲካዊ አለመረጋጋትን ወይም ግጭቶችን አይጋብዙም[5]፡፡ አገራቱም ከነዚህ የማንነት ልዩነቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ግጭቶች የሚጋፈጡት ችግሮች መጠንና ደረጃም ይለያያል፡፡

ከነዚህ የማንነት ልዩነቶች ውስጥ በብሔር /ቋንቋ ላይ መሠረት ያደረጉ ግጭቶች አንደኛው ነው፡፡ በብሔር/ቋንቋ ላይ ተመርኩዘው የሚነሱ ግጭቶች በአንዳንድ አገራት ወደ ፖለቲካ ግጭት ይለወጣሉ፡፡ በመሆኑም ችግሩን መፍታት የግድ አስፈላጊ ነው፤ አማራጭም የለም፡፡

በብሔር /ቋንቋ ልዩነት ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ማቻቻልና መምራት እንጂ ችግሩን እስከ ወዲያኛው ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ መፍታት እንደማይቻል የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ የዚህን አይነት ግጭት በተገቢው መንገድ በመምራት ችግሩን መቀነስ እንጂ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ አይቻልም፣ አይሞከርም፡፡ ታዲያ ዋነኛው ቁምነገር የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ነው፡፡

ችግሩን ለመፍታት ከሚቀርቡ አማራጭች ውስጥ አንዱ ተቋማዊ መፍትሄ ነው፡፡ የፖለቲካ ተቋማትን በማደራጀት በብሔር/ ቋንቋ ላይ የተመረኮዘ አለመረጋጋትን ወይም ግጭትን

[4] የትኛው ንድፍ ችግሩን ይቀርፈዋል? ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ የለም፡፡ ላይፓርትም ሆነ ሆሮዊትዝ አንዱ ያቀረበው ንድፍ ችግሩን ያባብሰዋል ከሚል ሙግት የትኛው በትክክል የችግሩ መፍትሄ ነው፤ ወይም ችግሩን የበለጠ ይቀንሰዋል በሚለው ላይ ስምምነት የለም፡፡

[5] ቁጥር 1፣ ገጽ 5 ይመለከቷል፡፡

በማቻቻል ችግሩን መቀነስ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ፖለቲካዊ ብሎም የሕግ ማዕቀፉን የሚመለከት ነው፡፡ የፖለቲካ ተቋማዊ አቅጣጫው (Political Institution) የዴሞክራሲ ንድፉን (the design of the democracy) የሚመለከት ሲሆን የሕግ ማዕቀፉ ደግሞ የሚወሰነው በሚነደፈውና ሥራ ላይ በሚውለው ሕገ-መንግሥት ነው፡፡

በርካታ ተቋማዊ አደረጃጀቶችና ንድፎች[6] በመፍትሔነት የቀረቡ ቢሆንም ሁለት ንድፎች (ሞዴሎች) በዋነኝነት ጎልተው ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ንድፎች ተነፃፃሪና ተወዳዳሪ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የስምምነት (ሥልጣን የማጋራት) ዴሞክራሲ (consociational democracy) ሲሆን፣ ሁለተኛው የማሳሳብ ሞዴል (Centripetalism) ነው፡፡[7]

## የምዕራባዊያን የዴሞክራሲ ንድፍ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ተገቢ አለመሆን

በአብዛኛው በምዕራብ አገሮች በተለይም በብሪታንያና በአሜሪካ በተግባር ላይ የዋለውና በስፋት የሚታወቀው የብዙሃን ዴሞክራሲ ስርዓት (Western Majoritarian Democracy) ነው፡፡ የምዕራባውያኑ የብዙሃን ዴሞክራሲ ሥርዓት የሕዝብ ተወካዮች በአብላጫ ድምፅ የምርጫ ስርዓት (Majority or Plurality Electoral system) የሚመረጡበትና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች በአብላጫ ድምፅ የሚወሰንበት ስርዓት ነው፡፡ የዌስት ሚኒስትር ሞዴል በመባልም ይታወቃል፡፡

የዚህ ሥርዓት መሠረቱ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች በብዙሃን ብልጫ ውሳኔ መስጠት ወይም ማሳለፍ ነው፡፡ ይህ የዴሞክራሲ ንድፍ (ሞዴል) ተግባራዊነትና መፍትሔ ሰጭነቱ በማሕበረሰብ ውስጥ ያሉ ልዩነቶች በብሔር/ቋንቋ/ ማንነት ላይ የተመሠረቱ ሳይሆን ጥቅምና ፍላጎት ላይ መሠረት ያደረገ ልዩነት ባለባቸው አገራት (ማህበረሰቦች) ነው፡፡[8]

የብዙሃን ዴሞክራሲ ሥርዓት በውድድር ፖለቲካ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ፓርቲዎች ፖሊሲዎቻቸውን ለህዝብ በማቅረብ ይወዳደራሉ፡፡ የብዙሃኑን ድጋፍ ያገኘው ፓርቲ መንግስት ይሆናል የተሸነፈው ደግሞ ተቃዋሚ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ የፖለቲካ ውድድሩ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ብዙ ጊዜ አያስከትልም፡፡ የተሸነፈው ፓርቲ ለሌላ ምርጫ ራሱን ያዘጋጃል እንጂ ስርዓቱን ለማወክ ወይም ለመገልበጥ አይንቀሳቀስም፡፡

ይህ የብዙሃን ዲሞክራሲ ሥርዓት እንዲሰራ ያስቻለው ወይም ግጭት ብዙ ግዜ የማይጠናወተው በሁለት መነሻ ሃሳቦች ላይ የተመሠረተ ወይም የተንጠለጠለ በመሆኑ ነው[9]፡፡ የመጀመሪያው ተቃዋሚዎች በምርጫ ቢሸነፉም ፍላጎትና ጥቅማቸውን የሚያራምድና የሚያስጠብቅ ነው፣ የሚሉት ሐሣብ ተቀባይነት ካገኘ ሥልጣን ላይ

[6] ከስምምነት ዴሞክራሲና (Consociational democracy) ከማሰሳብ ዴሞክራሲ ሞዴል (Centriptalism) በተጨማሪም ልዩነታቸውን ለማስመርም በጣም አስቸጋሪ የሆኑት እንደ Multiculturalism እና Territorial Pluralism የመሳሰሉትም እንደአማራጭ ግጭት መቀነሻ ወይም መፍቻ ይቀርባሉ፡፡ የሚከተለውን Yemlektu John McGarry et al, Integration or Accommodation? The enduring debate in conflict regulation in Constiutional Design in Divided Socities, oxford university presss, 2009, p. 51-67.

[7] ዝኒ ከማሁ ገጽ 51-67

[8] ቁጥር 1ን ገጽ 14-18 ይመለከቷል፡፡

[9] ዝኒ ከማሁ ገጽ 18

የመውጣት ዕድል ያላቸው መሆኑ ነው[10]፡፡ ሁለተኛው ገዢ ብዙሀን ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ስልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለመጨቆኛ አያውሉትም፤ የሚል መነሻ ሃሳብ ነው[11]፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ ጥምረት የሚመሰርቱትና ወይም አብላጫ የሚሆኑት ከጉዳይ ጉዳይ ስለሚለያይ ነው፡፡ በመሆኑም የምዕራባውያን ዴሞክራሲ የተመሠረተበት መነሻ እሳቤ ልዩነቶች በማንነት (identity cleavage) ሳይሆን በጥቅምና ፈላጎት (Crosscutting cleavage) ላይ የተመሠረቱና በዴሞክራሲያዊ አግባብ መስተናገድ የሚችሉ ናቸው በሚል አስተሳሰብ ላይ ነው፡፡

ይህ የብዙሃን ዴሞክራሲ ሥርዓት ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች የማይሰራበት ምክንያት እነዚህ ሁለት መነሻ እሳቤዎች በነዚህ ማሕበረሰቦች ውስጥ ስለማይኖሩ (ስለማይገኙ) ነው፡፡ በነዚህ ማሕበረሰቦች ውስጥ ያለው ልዩነት በማንነት ላይ (identity based cleavage) እንጂ የጥቅምና ፍላጐት ላይ ብቻ የተመረኮዘ አይደለም፡፡ በተከፋፈለ ማሕበረሰብ ውስጥ የሚገኙ አናሳዎች በፖለቲካ ውድድር ወደ ሥልጣን የሚመጡበት አግባብ ጠባብ ነው፤ ወይም የለም፡፡ በተከፋፈለ ማሕበረሰብ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚከተለው ቋሚና ዘላለማዊ አናሳነት ተብሎ ይገለፃል[12]፡፡ አናሳዎች ሥልጣን የማግኘት ተስፋቸው በጣም ጠባብ፤ ወይም ዜሮ ነው፡፡

አናሳዎች በምርጫ ስልጣን የሚይዙበት አጋጣሚ በጣም ትንሽ በመሆኑ የብዙሃን ዴሞክራሲ ሥርዓት የውድድር ፖለቲካ ንድፍ የተከፋፈሉ ማህበረሰብ ባለባቸው አገራት ሰላምን ሳይሆን ግጭትና አለመረጋጋትን የማስከተል ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደዘርፉ ምሁራን የምዕራባውያን የብዙሃን ዴሞክራሲ ሥርዓት ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች አለመረጋጋቱን ወይም ግጭቱን ከማባባስ የዘለለ ፋይዳ የለውም፡፡

በዚህም ምክንያት የምዕራባውያን የብዙሃን ዴሞክራሲ ሥርዓት ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ላለባቸው አገራት ተገቢ አይደለም ብለው ይከራከራሉ፡፡ እነዚህ አገራትም ይህንን እንዳይተገብሩ ያስጠነቅቃሉ፡፡

## የሕገመንግስት ንድፍ አማራጮች የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ላሉባቸው አገራት

ምሁራኑ የምዕራባዊያን የብዙሃን ዴሞክራሲ ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች የማይሠራና አደገኛ መሆኑን ቢስማሙም ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ተገቢ አማራጭ የሚሉት አንድ የዴሞክራሲ ንድፍ ግን የላቸውም፡፡ በብሔር /ቋንቋ ላይ የተመረኮዘ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ባላቸው አገሮች ችግሩን ለማቻቻልና ለመምራት ሁሉንም የሚያስማማ ተገቢ የሆነ የሕገመንግስት ንድፍ የለም፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ ከሚቀርቡ የሕገ-መንግስት ንድፎች ግልጽ ልዩነት ያላቸውና ተነፃፃሪ (ተወዳዳሪ) ሆነው የቀረቡት ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በአረንድ ላይፓርት የሚቀነቀነው የስምምነት (ስልጣን የማጋራት) ዴሞክራሲ (consociationalism) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ

---

[10] ዝኒ ከማሁ ገጽ 18

[11] ዝኒ ከማሁ ገጽ 19

[12] ዝኒ ከማሁ ገጽ 17

የማሳሳብ ዴሞክራሲ (centripetalism)[13] ነው፤ የዚህ ንድፍ አመንጭ ሮናልድ ሆሮዊትዝ ነው፡፡

የሁለቱም ንድፎች በብሄር/ቋንቋ ላይ የተመሠረተ ግጭት ያለና ተቋማዊ መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባ ነው፤ ከሚል መነሻ ሀሳብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ብሔር/ ቋንቋ ልዩነትን እውቅና ሰጥቶ መፍትሔ ከመስጠት ባሻገር ለመደፍጠጥ ወይም ልዩነት ለማጥፋት መሞከር ወይም ፖለቲካዊ እውቅና አለመስጠት አደገኛ መሆኑን ያሰምራሉ[14]፡፡

ላይፓርትና ሆሮዊትዝ የምዕራባዊያን ብዙሃን ዴሞክራሲ ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ተገቢ አለመሆኑን ቢስማሙም ያቀረቧቸው አማራጭ የዴሞክራሲ ንድፎች ፍጹም የተለያዩ ናቸው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ላይፓርት የስምምነት (ስልጣን የማጋራት) ዴሞክራሲን (consociationalism) በመደገፍ የሚያቀርብ ሲሆን በሆሮዊትዝ የቀረበውን አማራጭ ያጣጥላል፡፡

ሆሮዊትዝ በበኩሉ ላይፓርት ያቀረበው የዴሞክራሲ ሞዴል ችግሩን የማይፈታና ይብሱንም የብሔር ግጭት የሚያባብስ ነው፤ ብሎ ይከራከራል፡፡ የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ያላቸው አማራጭ የማሳሳብ ደሞክራሲ ሞዴል (centripetalism) ብቻ እንደሆነ ይሰብካል፡፡

ሁለቱም በጣም የተራራቀ የዴሞክራሲ ንድፍ እንዲኖራቸው የሆነበት ምክንያት በብሄር/ ቋንቋ ማንነትና ልዩነት ላይ ተመርኩዞ ለሚነሳ ፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት የሚፈታው የብሔር ልሂቃንን የሚያስማማ ወይም የሚወከሉበት ሥርዓት ነው? ወይስ የብሄር ልሂቃንን ሚና በማሳነስና ቦታ ባለመስጠት? በሚለው ላይ ከሚነሣ የተለያየ ግምት ነው፡፡[15] ላይፓርት የብሄር ልሂቃንን ተመጣጣኝ ውክልና የሚያስረግጥ ሥርዓት በብሔር /ቋንቋ ላይ ተመስርቶ ሊነሳ የሚችል የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት መቀነስ ያስችላል፤ ብሎ ያምናል[16]፡፡ ሆሮዊትዝ በበኩሉ የዴሞክራሲ ንድፍ የብሔር/ቋንቋ ልሂቃንን አስፈላጊነትና ሚና ማቀጨጭ ብቸኛው በተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ውስጥ ሊነሣ የሚችለውን በብሔር /ቋንቋ ላይ የተመሠረተ ግጭትን መቀነሻ ቁልፍ ጉዳይ ያደርጋል[17]፡፡

## 2.1. የላይፓርት የስምምነት/ስልጣን የማጋራት/ ዴሞክራሲ ንድፍ (Consociationalism)

ይህ የዴሞክራሲ ንድፍ እላይ እንደተጠቀሰው በላይፓርት የሚቀነቀነው ነው፡፡ የስምምነት/ስልጣን የማጋራት ዴሞክራሲ መሠረታዊ ሐሣብ የብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች የአስፈፃሚውን ሥልጣን ማጋራት (Executive Power-sharing) ሁነኛ መገለጫው ነው፡፡

የስምምነት/ ስልጣንን የማጋራት ዴሞክራሲ (Consociationalism) ቀዳሚ መገለጫዎችና (primary attributes) ተከታይ መለያዎች (secondary attributes) አሉት[18]፡፡ ቀዳሚ

---

13 ቁጥር 1 እና 4ን ይመለከቷል፡፡

14 ዝኒ ከማሁ ቁጥር 1 ገጽ 26፤ ቁጥር 4 ገጽ 53-59 ይመለከቷል፡፡

15 ቁጥር 1፣ ገጽ 25፣ይመለከቷል፡፡

16 ዝኒ ከማሁ

17 ዝኒ ከማሁ

18 Lijphart Arend Constiutional Design for Divided Societies, *Journal of Democracy Volume 15, Number 2 April 2004 p.97*

መገለጫዎቹ (primary attributes) ራሳቸው ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የተለያዩ የብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች ያቀፈ ሥልጣን መጋራት በተለይ የአስፈፃሚ ስልጣን ማጋራት (executive power-sharing) ሲሆን፣ ሁለተኛው ብሔር/ቋንቋ ቡድኖች በውስጥ ጉዳዮች ራስን የማስተዳደር ነፃነት (regional autonomy) ነው[19]፡፡ ተከታይ መለያዎቹ (secondary attributes) ብሎ የሚያስቀምጣቸው የብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች በተለይም አናሣዎች ጥቅምና ፍላጐታቸውን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት (veto power) እና ተመጣጣኝ ውክልና (proportional representation) ማግኘት ናቸው[20]፡፡

ላይፓርት አላይ ካመለከታቸው ቀዳሚና ተከታይ መገለጫዎች በተጨማሪ የሁለት ምክር ቤቶች መኖር (Bicameralism) እና የሕግ ሥርዓት ብዙሃነትን (Legal Pluralism) ተጨማሪ የንድፉ አካል አድርጎ ያቀርባል[21]፡፡

ላይፓርት በአንድ ጽሁፉ የተከፋፈሉ ማሕበረሰብ ያለባቸው አገራት ሕገ-መንግስት የሚፅፉ ወይም የሚቀርጹ ሰዎች ምን አይነት ዝርዝር ተቋማት ሊዘረጉ ይገባቸዋል፤ የሚላቸውን ጥርት ባለ መልኩ አመላክቷል[22]፡፡ ይህም ከመንግስት ቅርጹ እስከ ምርጫ ሥርዓት ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡

አንደኛው የሕግ አውጭው ምክርቤት የሚመረጡበትን የምርጫ ሥርዓት ይመለከታል[23]፡፡ አባላቱ የሚመረጡበት ከላይ እንደተገለፀው በተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት መሆን አለበት፡፡

ሁለተኛው ላይፓርት ስልጣን የማጋራት ዴሞክራሲ ቀዳሚ መገለጫ ያለው የብሔር/ቋንቋ ቡድኖች በፓለቲካ ውስጥ አሳታፊነትን ሆኖ፣ ዋናው የአስፈጻሚ ሥልጣንን መጋራት ነው[24]፡፡ የአስፈጻሚው ስልጣን መጋራት ሙሉ ለሙሉ ሁሉንም የብሔር/ቋንቋ ቡድኖች የተወከሉበት ወይም ዋና ዋና የብሔር/ቋንቋ ቡድኖች የተወከሉበት ወይም ወሳኝ የሆኑ የብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች የተወከሉበት ሆኖ ሊዋቀር ይችላል፡፡ እያንዳንዱ አገር ተገቢ ነው፤ የሚለውን አማራጭ መዘርጋት የሚችል ሲሆን የአስፈጻሚው ሥልጣንን የብሔር/ቋንቋ ቡድኖች የሚጋሩት እስከሆነ ድረስ ላይፖርት ሙሉ ለሙሉ፣ ዋና ዋና ወይም ወሳኝ ጥምር የብሔር/ቋንቋ ቡድኖች ውክልና መቼና ለምን አይነት የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ተገቢ ነው? የሚለውን አላሳየም፡፡

ሦስተኛው ሥርዓተ-መንግስትን ይመለከታል፡፡[25] ላይፓርት ከፕሬዚደንታዊ ወይም ከፊል ፕሬዚደንታዊ ሥርዓተመንግስት ይልቅ ፓርላሜንታዊ ሥርዓተ-መንግስት የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ላለባቸው አስፈላጊ ነው፤ ብሎ ይከራከራል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ፓርላሜንታዊ ሥርዓተ-መንግስት ሥልጣንን ለማጋራት ከሌሎቹ አማራጮች የተመቻቸ በመሆኑ ነው፡፡

---

19 ዝኒ ከማሁ ገጽ 25 እንዲሁም ቁጥር 1 ገጽ 18-19

20 ቁጥር 1 ገጽ 18-19

21 ዝኒ ከማሁ ገጽ 18-19

22 ዝኒ ከማሁ ገጽ 99-106

23 ዝኒ ከማሁ ገጽ 100

24 ዝኒ ከማሁ ገጽ 103

25 ዝኒ ከማሁ ገጽ 101

ፓርላሜንታዊ ሥርዓተ-መንግስት ከፕሬዚደንታዊ ሥርዓተ-መንግስት አንፃር ቶሎ የመበተን አደጋ የተጋረጠበት ቢሆንም ላይፓርት ይህ በጣም አሳሳቢ ችግር እንዳልሆነና የተለያዩ መፍትሔዎች ማቅረብ እንደሚቻል ይናገራል፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ ችግሩን በጀርመን ሕገ-መንግስት እነደተደነገገው ሕግ አውጪው አስፈፃሚውን ከስልጣን የሚያሰናብተው በምትኩ ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሾም ነው፤ የሚለውን እንደአማራጭ ማቅረብ እንደሚቻል ይገልጻል[26]፡፡

አራተኛው የርዕሰ-ብሔር አመራረጥን ይመለከታል[27]፡፡ የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ባለባቸው አገራት ላይፓርት የሚመክረው ርዕሰ-ብሔር በቀጥታ እንደ ፕሬዚደንታዊ ሥርዓተ-መንግስት በሕዝቡ መመረጥ እንደሌለበትና ለፕሬዚደንቱ ስልጣኑም በጣም ትንሽና የጌጥ ሥልጣን (Ceremonial powers) ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህን የሚልበት ምክንያት ፕሬዚደንቱ በቀጥታ ከተመረጠ ዴሞክራሲያው ተቀባይነት (democratic legitimacy) ስለሚያስገኝለትና ትልቅ ስልጣን ከተሰጠው በሂደት ሥርዓቱ ወደ ከፊል ፕሬዚደንታዊ ሥርዓተ-መንግስትነት (Semi-presidentialism) የማዘንበል ወይም የመቀየር አደጋ ስለሚያስከትል ነው[28]፡፡

አምስተኛው የፖለቲካ ሥርዓቱን በተመለከተ ላይፓርት የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ባሉበት አገር የሚመክረው እንደየአገራቱ ሁናቴ ፌዴራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት በመዘርጋት ወይም ሥልጣንን ወደታች በማውረድ (Decentralization) ነው[29]፡፡ የማህበረሰቡ ጂኦግራፊያዊ አሰፋፈር በአንድ አካባቢ የተወሰነ ከሆነ ለማህበረሰቡ አካባቢያዊ የአስተዳደር ነጻነት ለመስጠት ፌደራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት በጣም ተመራጭ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ የፌደራል ሥርዓቱ ሥልጣንን ወደታች በደንብ ያወረደና አባል ክልላቱ በተቻለ መጠን መጠናቸው (የቆዳ ስፋትና የህዝብ ቁጥርን ይመለከታል) ትንሽ ቢሆን ይመረጣል፡፡ የአባል ክልላቱ መጠን ትንሽ ይሁን የሚልበት በሁለት ምክንያት ነው[30]፡፡ አንደኛው ማህበረሰቡ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የመሆን ዕድልን ስለሚጨምር ሲሆን ሁለተኛው ትልልቅ አባል ክልላት ካሉ በፌደራል መንግስት ላይ ሊያሳርፉ የሚችሉትን ተፅዕኖ መቀነስ ስለሚያስችል ነው[31]፡፡

ስድስተኛው ማህበረሰቡ በአንድ መልካምድራዊ አካባቢ የማይገኝ ከሆነ ራስን የማስተዳደር ነፃነትን ግዛት ላይ መሰረት ባላደረገ መልኩ ማደራጀት እንደሚቻልና እንደሚገባ ያመላክታል[32]፡፡ ለዚህም በህንድ፣ በቤልጂየምና በኔዘርላንድ የመንግስት እኩል የገንዘብ እርዳታ ለሁሉም ትምህርትቤቶች መስጠት፤ የሐይማኖት ቡድኖችን ትምህርትቤቶችን ለመቆጣጠር ያላቸውን ፍላጎት የሚመልስና ምንም እንኳን መንግስትና ሐይማኖት መለያየት

[26] ዝኒ ከማሁ ገጽ 101
[27] ቁጥር 17 ይመልከቱገጽ 104
[28] ዝኒ ከማሁ ገጽ 104
[29] ዝኒ ከማሁ ገጽ 104
[30] ዝኒ ከማሁ ገጽ 105
[31] ዝኒ ከማሁ ገጽ 105
[32] ዝኒ ከማሁ ገጽ 105

አለባቸው፤ የሚለውን መርህ የሚጥስ ቢሆንም መንግስትን በሐይማኖት ጉዳይ ገለልተኛ ያደርገዋል፤ ይላል[33]፡፡

ሰባተኛው ከአስፈፃሚውና ሕግ አውጪው ምክርቤት ውጪ ያለውን ሥልጣንን መጋራት ይመለከታል[34]፡፡ የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ባሉባቸው አገራት በአስፈፃሚውና ሕግ አውጪው ምክርቤት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ዘርፍም ሰፋ ያለ ውክልና መኖሩን ማረጋገጥ እንደሚገባ ላይፓርት ይከራከራል፡፡ በመንግስት ስራዎች /በሲቪል ሰረቪስ/፣ በፖሊስ፣በመከላከያ እና በፍርድ ቤትም ውስጥ ሰፋ ያለ ውክልና ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.2. የማሳሳብ ዴሞክራሲ ንድፍ (Centriptalism)

ይህ የዴሞክራሲ ሞዴል/ንድፍ/ የሚያተኩረው በማሳሳብ፣ አንድ ላይ በማምጣት ወይም በማዕከላዊነት ላይ ነው[35]፡፡ መነሻ እሳቤው በተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ያለው በብሔር /ቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ግጭት የሚፈታው ላይፓርት እንደሚለው ልሂቃኑን ሥልጣን በማጋራት ሳይሆን የልሂቃኑ ሚና መቀነስና ፖርቲዎችን ከብሔርተኮር አጀንዳ ላይ አውጥቶ ወደ ማዕከላዊ አጀንዳ መግፋት ወይም ማዕከላዊ አጀንዳ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፤ በሚለው ላይ ነው፡፡

ሆሮዊትዝ በላይፓርት የቀረበውን የማስማማት/የስልጣን መጋራት/ዴሞክራሲ (consociational arrangment) ልሂቃኑን በማቻቻል በብሔር/ቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ግጭትን መቀነስ ይቻላል፤ የሚለውን ይተቻል፡፡ እንደሆሮዊትዝ ከሆነ ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ያባብሱታል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የዴሞክራሲ ንድፉና የምርጫ ሥርዓቱ ልሂቃኑ የሚወክሉትን ብሄር/ ቋንቋ ቡድን ጥቅምና ፍላጐት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ በመሆኑ ነው[36]፡፡ በምርጫም ወቅት ፓርቲዎች ብሔር-ተኮር ጥቅምና ፍላጐት ላይ እንጂ የጋራ ጉዳዮች (ጥቅምና ፍላጐት) ላይ እንዳያተኩሩ ያደርጋል፡፡ ይህ በሂደት ብሔር-ተኮር ጥቅምና ፈላጐት በማተኮር የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ውስጥ ያለውን ልዩነት የበለጠ ያሰፈዋል፤ ሲከፋም ወደ ግጭት ያመራል፤ የሚል ነው፡፡

ሆሮዊትዝ ያቀረበው የተሳሳቢነት (ወደየጋራ አጀንዳ የመሳብ) ዴሞክራሲ ንድፍ (centripetalism) የምርጫ ስርዓቱን በመጠቀም ፖርቲዎች ከብሔር-ተኮር ጥቅምና ፍላጐት ይልቅ ወደ ጋራ የሆኑ ጥቅምና ፍላጐቶችን እንዲመጡ መገፋፋት (incentive) ነው፡፡ በመሆኑም ፓርቲዎቹን ወደ ማዕከላዊ አጀንዳ በማምጣት ላይ ያለመ ነው፡፡ ይህን ማሳካት የሚቻለው በለዘብተኛ የብሔር ልሂቃን ነው፡፡ እንደ ሆሮዊትዝ ገለጻ የላይፓርት ንድፍ የብሔር ሊሂቃኑን ብሔርተኮር በመሆን ለዘብተኛ ከመሆን ይልቅ ጽንፈኛ እንዲሆኑ ያበረታታል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ማዕከላዊ ወይም ለዘብተኛ አቋም የሚይዙ ፓርቲዎችና ልሂቃን አክራሪ በሆኑ ፓርቲዎች ከባድ ፉክክር ይገጥማቸዋል[37]፡፡ ብሔር-ተኮር አጀንዳዎች ማራገብ የመመረጥ እድል ስለሚያሰፉና ለዘብተኛነት የመመረጥ እድል

[33] ዝኒ ከማሁ ገጽ 105

[34] ዝኒ ከማሁ ገጽ 105-106

[35] ቁጥር 4 ገጽ 53 ይመለከቷል፡፡

[36] ቁጥር 1፣ ግጽ 21 ይመለከቷል፡፡

[37] ዝኒ ከማሁ ገጽ 21-22

ስለሚያጠብ፤ በሂደት አክራሪ አጀንዳ የሚያራምዱ ፖርቲዎች ለዘብተኛዎችን ሚናቸውን አቀጭጨው ከጨዋታ ውጭ ሊያደርጓቸው ይችላሉ፡፡

በመሆኑም ሂደቱ አክራሪ አቋም የሚያራምዱ ፓርቲዎችንና ልሂቃንን እያጐላ ልዩነቶች እያገነነ በብሔር /ቋንቋ ላይ የተመሠረተ ግጭቱ ጥልቀትና ሥፋቱ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም እንደሆሮዊትዝ ገለጻ የዴሞክራሲ ንድፉ ለዘብተኛ ልሂቃን አሸናፊ የሚሆኑበትና አክራሪ/ ጽንፈኛ ልሂቃን አስፈላጊነትና ሚናን ቦታ የሚያሳጣ መሆን አለበት፤ ብሎ ይከራከራል፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁነኛ መሣሪያ አድርጐ ሆሮዊትዝ የሚወስደው የምርጫ ሥርዓቱን ነው፡፡

የምርጫ ሥርዓቱ አቀራረጽ ከብሔር/ቋንቋ ይልቅ የጋራ ጥቅምና ፈላጐት የሚያራምዱ ፓርቲዎችንና ልሂቃንን የሚሸልም፣ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡ የምርጫ ሥርዓቱ አክራሪ ፓርቲዎችንና ልሂቃንን የሚያኮስሰው ከራሳቸው ብሔር/ ቋንቋ ቡድን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ብሔር/ቋንቋ ቡድንም ድምጽ ማግኘት እንደሚችሉና እንደሚገባቸው ሆኖ ሲቀረጽ ነው፡፡ ከብሔር/ቋንቋ ቡድናቸው ውጭ ከሆኑ ማሕበረሰቦች ድምጽ ለማግኘት ደግሞ አክራሪ ፓሊሲዎቻቸውንና አጀንዳዎቻቸውን እንዲሞርዱና እንዲያለዝቡ ይገደዳሉ፡፡ በመሆኑም እንደ ሆሮዊትዝ ገለፃ ሂደቱ ፖርቲዎችና ልሂቃኑን አክራሪ አቋሞችና አጀንዳዎች ወደማዕከላዊ/ የጋራ አጀንዳዎች እንዲመጡ ይገፋፋቸዋል፡፡ ስለሆነም በብሔር/ ቋንቋ ለይ የሚመሠረቱ ግጭቶች በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳሉ፡፡

ካሉት የምርጫ ሥርዓቶች ይህንን ግብ ያሳካል ብሎ ሆሮዊትዝ የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች እንዲጠቀሙበት የሚያሣስበው አማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት (Alternative vote) የሚባለውን ነው[38]፡፡ ይህ የምርጫ ሥርዓት ሳይፓርት የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ሊኖራቸው ይገባል ብሎ፤ ካቀረበው የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት (proportional representation) በእጅጉ የተለየ ነው፡፡

አማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት በብዙሃን የምርጫ ሥርዓት (Majority or Plurality electoral system) ውስጥ የሚመደብ ነው[39]፡፡ የብዙሃን የምርጫ ሥርዓት (Majority or Plurality electoral system) መለያው ከተወዳዳሪዎች ውስጥ አብላጫ ድምጽ ያገኘው አሸናፊ የሚሆንበት ሥርዓት ነው[40]፡፡

አማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት (Alternative vote) በብዙሃን የምርጫ ሥርዓት ውስጥ የሚመደብ ቢሆንም ለየት ያለ ይዘት አለው፡፡ በአማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት (Alternative vote) ተወደዳሪው አሸናፊ የሚሆነው አብላጫ ድምጽ ስላገኘ ሳይሆን ከግማሽ በላይ ድምጽ (50%+1) ካገኘ ነው[41]፡፡ በዚህ የምርጫ ሥርዓት መራጮች አንድ

---

[38] ዝኒ ከማሁ ገጽ 21

[39] Reynolds Andew et al, Electoral System Design: The New International IDEA Handbook , Stockholm, 2005, p.35

[40] ዝኒ ከማሁ ገጽ 35

[41] ዝኒ ከማሁ ገጽ 47 አማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት በእጅጉ ከሁለት ዙር የምርጫ ሥርዓት ጋር የሚመሳሰል ሆኖ የሚለያቸው በሁለት ዙር የምርጫ ሥርዓት ምርጫው እንደስሙ በሁለት ዙር የሚካሄድ መሆኑ ነው፡፡ በአማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት ግን ምርጫውን ሁለት ዙር ማካሄድ ሳያስፈልግ መራጮች በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ እንደየደረጃቸው ተወደደሪዎቹን እንደመርጡ ይደረጋል፡፡

የሚፈልጉትን ተወዳዳሪ ብቻ ሳይሆን የሚመርጡት በምርጫ መስጫ ወረቀቱ ላይ ተወደዳሪዎቹን ቁጥር በመስጠት እንደ ምርጫ ፍላጐታቸው በደረጃ ያመለክታሉ፡፡ ከተሰጠው ድምጽ ውስጥ ከግማሽ በላይ ድምጽ በአንደኛ ደረጃ የተመረጠ ካለ አሸናፊ ይሆናል፡፡ ከግማሽ በላይ ድምጽ ያገኘ ተወደዳሪ ከሌለ አነስተኛ ድምፅ ያገኘው ተወዳዳሪ ይወገድና የመራጮች ሁለተኛ ደረጃ ምርጫቸው ከፍ ያለ ላገኙት ይደመርላቸዋል፡፡ በዚህ ሂደት ድምጹ እየተደመረ ከግማሽ በላይ ድምጽ ያገኘው ተወዳዳሪ አሸናፊ ይሆናል፡፡

እንደ ሆሮዊትዝ አገላለጽ አማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት (Alternative vote) ከሌሎች የምርጫ ዓይነቶች የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ተመራጭ/ የተሻለ የሚያደርገው ፖርቲዎችንና ልሂቃኑን የምርጫ አጀንዳቸውንና ፖሊሲዎቻቸውን ብሔር/ቋንቋ ዘለል ሆኖ ወደ ጋራ ጥቅምና ፍላጐት የሚገፋቸው ስለሆነ ነው[42]፡፡ በምርጫ ስርዓቱ ተመራጩ/ተወዳዳሪው ከግማሽ በላይ ድምጽ ማግኘት ስለሚገባውና አክራሪ አጀንዳ ማራመዱ ድምጽ የማግኘት እድሉን ስለሚያጠበው የጋራ ጥቅምና ፍላጐት ጉዳዩች ላይ እንዲያተኮር ያደርገዋል፡፡ በዚህ ምርጫ ሥርዓት ለማሸነፍ/ድምጽ ለማግኘት ከብሔር/ቋንቋ ውጩ ያሉ ማሕበረሰቦች ድምጽ ማግኘት ይገባዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው ፓርቲዎችና የብሔር ልሂቃን የሚያራምዱት አጀንዳ ከተወዳዳሪው/ከተመራጩ ብሔር/ቋንቋ ውጪ ያሉ ማሕበረሰቦችን ጥቅምና ፍላጐት የሚያንፀባርቅ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በዚህ መልኩ የምርጫ ሥርዓቱ ፖርቲዎችንና ልሂቃንን ወደ ማዕከልና አቻቻይ አጀንዳ በመግፋት አክራሪ አጀንዳ የሚያራምዱ ፓርቲዎችንና ልሂቃንን ያዳክማል፤ ያኮስምናል፡፡ አክራሪ ፖርቲዎችና ልሂቃን ለዘብተኛ ፖሊሲዎችን እንዲቀበሉና እንዲያራምዱ በማመቻቸት በብሔር/ ቋንቋ ላይ የተመሠረተ ግጭት እንዲቀንስ ይረዳል[43]፡፡

በተለይም በናይጀሪያ ያለውን ፕሬዝደንቱን የሚመረጥበት መንገድ መከተል ለተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በናይጀሪያ ሕገ-መንግስት መሠረት ፕሬዚደንቱ ከግማሽ በላይ ድምጽ ማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ 25% የሚሆን የክልሎች ድምጽ ማግኘት ይጠበቅበታል[44]፡፡ ይህ ድንጋጌ ፕሬዚደንቱ የመመረጥ ዕድሉን ለማስፋት ድምጽ አገኛለሁ፤ ብሎ ከሚያገኝበት የራሱ ብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች የሚገኙበት ክልሎችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ድምጽ እንዲሰጡት የነሱን ጥቅምና ፍላጐት የሚያራምድ ፖሊሲ/ አጀንዳ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆሮዊትዝም አጽኖት የሚሰጠው በምርጫ ሥርዓቱ አስታራቂነትና አለዛቢነት ላይ ነው፡፡

አሀዳዊ ወይም ፌደራላዊ የመንግሥት ሥርዓትን በሚመለከት ሆሮዊትዝ አሀዳዊ ሥርዓት-መንግስት የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ሊኖራቸው ይገባል ብሎ ባይከራከርም የፌደራል ሥርዓት-መንግስት አስታራቂነትና አለዛቢነት ጥቅምን ከግንዛቤ በመውሰድ የተከፋፈለ ማሕበረሰቦች ይህን ሥርዓት-መንግስት እንዲያቋቁሙ ያበረታታል[45]፡፡ የፌደራል ሥርዓት-

---

[42] ቁጥር 1 ይመልከቱ ገጽ 21

[43] ዝኒ ከማሁ ገጽ 21-26

[44] ቁጥር 4 ገጽ 54 እንዲሁም የ1999 (የአውሮፓ ካላንደር) የናይጀሪያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት ክፍል 133 እና 134ን ይመለከቷል፡፡.

[45] ዝኒ ከማሁ

መንግስት ሥልጣንን ከማዕከል ወደክልል ለመውሰድ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑም ይህንን ሥርዓተ-መንግሥት ይደግፋል፡፡

## 3. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ንድፍ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት ዋና አጀንዳ/ ዓላማ በብሔር/ቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ለመፍታት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ሕገ-መንግስቱ የተቀረፀበትና የፀደቀበት ጊዜና ሁኔታም፣ አገሪቱ ብሔር-ተኮር የነፃነት ትግል ሲያካሂዱ የነበሩ ቡድኖች ማዕከላዊ መንግስትን በ1983 ዓ.ም አሸንፈው ከወጡ በኋላ መሆኑ ሕገ-መንግሥቱ እንደ ዋነኛ በብሄር/ ቋንቋ ማንነት ላይ ተመርኮዞ ለሚነሳ ግጭት እንደ መፍቻ መንገድ ለመወሰዱ በቂ ማስረጃ ነው[46]፡፡

ከዚህም በላይ ሕገ-መንግስቱ ከመግቢያው ጀምሮ አንኳር አንኳር የሚባሉ አንቀጾቹ በዚህ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ መሆናቸው አሌ አይባልም፡፡ የሕገ-መንግስቱ ምሰሶ የቆመው በብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች ጥቅምና ፈላጎት ነው፤ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህ የሕገ-መንግስቱ የማዕዘን ድንጋጌ ተብሎ ከሚወሰደው አንቀጽ 39 ጀምሮ መግቢያው፣ አንቀጽ 8፣ አንቀጽ 47፣ አንቀጽ 48፣ አንቀጽ 61 እንደሁም በነዚህ ላይ ተንተርሰው በፌደራልና ክልል መንግስታት ስላለው የሥልጣን ክፍፍል የሚያውጁት አንቀጾች፤ 50፣ 51፣ 52፣ 55፣ 96፣ 97፣ 98፣ 99 ሕገ-መንገስቱ የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ የተከፋፈሉ ማሕበረሰብ የነበረና መሆኑን፤ በኢትዮጵያ የነበረውና ያለው ግጭት ብሔር/ቋንቋ ይዘት ነበረው፤ እንዲሁም አለው፤ ከሚል መነሻ ሐሣብ የተነሳ መሆኑን መመልከትና መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህም ሕገ-መንግስቱ ፖለቲካዊ ፋይዳው ከፍተኛ መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል፤ ብሎ የወሰደው በብሔር/ቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ግጭት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ማመሳሰል/ ልዩነትን ማጥፋት ፓሊሲ (Assimilation) እንዲሁም ማዋሃድ (Integration) ፓሊሲ ብሔር/ቋንቋ ላይ የተመሠረተ ግጭት ለመፍታት እንደ አማራጭ ፖሊሲ ያልተቀበለውና እንዲያውም የማመሳሰል ወይም ማዋሃድ ፖሊሲ በገዢው ፓርቲና በሌሎችም በኢትዮጵያ ያሉ ብሄረሰቦችን ማንነትን ለማጥፋት የታቀደ ሴራ ተደርጎ የተሰበከና አሁን ይህንን ማንሳት የተኮነነ/ነውር (taboo) ሆኗል፡፡ በመሆኑም ሕገ-መንገሥቱ በብሔር/ቋንቋ የተመረኮዘ ልዩነት ማስታረቂያው፤ የማቻቻል ፖሊሲ (Accomodation) ብቻ እንደሆነ ያቀርባል፡፡

### 3.1. የሕገ-መንገስቱ የማቻቻል ፖሊሲና ስትራቴጂ

የኤ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት መሠረቱ በብሔር፣ ብሐረሰብ፣ ሕዝብ ማንነት ላይ የተገነባ ነው፡፡ መነሻውና ማጠንጠኛውም የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጥቅምና ፍላጐት ላይ ነው፡፡ የማዕዘን ድንጋጌዩም የራስን እድል በራስ መወሰን መብት ነው፡፡ ሕገ-መንግስቱ የቆመበት፣ የሚሠራበት፣ የሚፈርስበትም በብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ፈቃድና ፍላጐት ላይ ነው፡፡

---

[46] ደርግን ከስልጣን ሲወርድ ብሄርተኮር ከነበሩት ድርጅቶች ውስጥ ሕ.ወ.ሀት (የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት፣ የኤርትራ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት፣ ኦ.ነ.ግ (የኦሮሞ ሕዝብ ነፃ አውጭ ድርጅት) ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

የሕገ-መንግስቱ በብሔር/ቋንቋ ማንነት ላይ የተመሠረተ አለመረጋጋት ወይም ግጭት መፍቻ ቁልፍ የራስን እድል በራስ መወሰን መብት የላይ የቆመ ነው፡፡ የሕገመንግስቱና የዴሞክራሲው ንድፍ፣ ቅርጽና ይዘት የሚፈሰው ከዚሁ ከብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሐዝቦች የራስን እድል በራስ መወሰን መብት ነው፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ ብሔር ብሔረሰቦችና፣ ሕዝቦች ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤትነት ደንግጓል[47]፡፡ የሕገ-መንግሥቱ መግቢያ የሚጀምረው እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብሎ ሳይሆን እኛ የኢትዮጵያ ብሔርብሔረሰቦችና ሕዝቦች… ብሎ ነው፡፡ ሉአላዊ ስልጣን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንደ ቡድን እንጂ ሉዓላዊ ስልጣን፤ የአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተደምሮም እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሕገ-መንግሥት መግቢያ የተገለጸበት ዓረፍተ-ነገር የቃልኪዳን ስምምነቱ አባላት ግለሰቦች በድምር ሳይሆን ብሔር ብሐረሰቦችና ሕዝቦች ብቻ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሰሪዎችም ሆኖ አፍራሾች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸው፡፡ የመግቢያው ዓረፍተ-ነገር ሆነ ከላይ የተገለጹት ሌሎች የተለያዩ አንቀጾች የሚያስረግጡት ይሄንን ነው፡፡

ሁለተኛ የሕገ-መንግሥቱ መገለጫ ብሔር-ተኮር የፌደራል ሥርዓት-መንግስት ማቋቋሙ ነው፡፡ ይህ የሚያሰኘው በአንቀጽ 47 የተዘረዘሩት አባል ክልላት በዋነኛነት በብሔር ላይ የተመረኮዙ መሆናቸው ነው፡፡ በርግጥ በአገሪቱ ከሰማንያ የማያንሱ የብሔር/ ቋንቋ ቡድኖች እንደሚኖሩ ቢገመትም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት እያንዳንዱ ብሔር/ ቋንቋ ቡድን ክልል አድርጐ አላደራጀም፡፡ ነገር ግን በንድፈ-ሀሳብም ሆነ በሕገ-መንግስቱ ደረጃ ሁሉም ብሔር/ ቋንቋ ቡድን የራሱን ክልል መመስረት የሚያረጋግጥ በመሆኑ እንዲሁም የድንበር ማካለል ውስጥ አንደኛው መስፈርት ማንነትን ማድረጉ ሲታይ ብሔር-ተኮር የፌደራል ስርዓት የገነባ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ሦስተኛ ልዩ የሕገ-መንገሥቱ መገለጫና በብሔር/ ቋንቋ መሠረት ያደረገ ግጭትን መፍቻ አድርጐ የወሰደው የራስን እድል በራስ ማስተዳደር አካል ወይም ተቀጥላ ተደርጐ ሊወሰድ የሚችለው የመገንጠል መብትን ማረጋገጡ ነው[48]፡፡

ከላይ ከተገለጹት ዋነኛ የሕገ-መንግስቱ መሠረታዊ በብሔር/ቋንቋ ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ ግጭት መፍቻ ስትራቴጂዎች በተጨማሪ ሕገ-መንግስቱ ያቋቋመው ሥርዓተ-መንገሥት ፖርላሜንታዊ ነው[49]፡፡ የምርጫ ሥርዓቱም በግልጽ በሕገ-መንግስቱ የተመለከተ ሲሆን ካሉት የምርጫ ሥርዓት አይነቶች የአብላጫ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት እንደሆነ ደንግጓል[50]፡፡

[47] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስትን አንቀፅ 8 ይመለከቷል፡፡ የሕገመንግሥቱ መግቢያ፣ አንቀጽ 8፣ አንቀጽ 39 እና አንቀጽ 47 ተነጣጥለው የማይታዩ ናቸው፡፡

[48] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀፅ 39 ይመለከቷል፡፡

[49] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀፅ 45፣ 69-77 ይመለከቷል፡፡

[50] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 54(2)

ከላይ እንደተገለጸው ሕገ-መንግስቱ ከአሀዳዊ ሥርዓት ይልቅ ፌደራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት መርጧል[51]። የመንግስት ስልጣንም በፌዴራልና በክልል መንግስታት መካከል አከፋፍሏል። የሥልጣን ክፍፍሉ የገቢ ምንጮችንም ይመለከታል[52]።

ሕገ-መንግስቱ ሁለት ምክርቤቶች እንዳሉት ቢደነገግም ሁለቱም እኩል ሥልጣን የላቸውም። በሕገ-መንግስቱ መሠረት የታችኛው ምክርቤት የተወካዮች ምክርቤት ነው። ይህ ምክርቤት የተዋቀረው በሕዝብ በቀጥታ በአብላጫ የምርጫ ሥርዓት በተመረጡ ተወካዮች ሲሆን የምክርቤቱ ሥልጣን ለፌደራሉ መንግስት በተሰጡት ሥልጣኖች ላይ ሕግ ማውጣት ነው[53]። አስፈጻሚው የሚወጣውና የሚዋቀረውም ከዚሁ ምክርቤት ነው[54]።

ሁለተኛው ምክርቤት የፌደሬሽን ምክርቤት ሲሆን የብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ተወካዮች የተዋቀረ ምክርቤት ነው[55]። በፌደራሉ ደረጃ በዋነኝነት በፌዴሬሽን ምክርቤት ውስጥ የብሔር ብሔረሰብ፣ ሕዝቦች የመወከል መብት ነው። እንደ ሕገ-መንግስቱ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ፣ ሕዝብ አንዳንድ ተወካይ የሚኖረው ሲሆን ተጨማሪ አንድ ሚሊዮን የሕዝብ ብዛት ያለው ብሔር ብሔረሰብ፣ ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ተወካይ ይኖረዋል።[56]

ሕገ-መንገስቱ የብሔር ብሔረሰብ፣ ሕዝቦች ተመጣጣኝ ውክልና በዚህ መልኩ እንደሚያገኙ ያመላክት እንጂ የፌዴሬሽን ምክርቤቱ እኩል ሕግ የማውጣት ስልጣን ከተወካዮች ምክርቤት ጋር እንዲኖረው ስላልተደረገ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዚህ መብት አኳያ የመጠቀም መብታቸው ውጤታማነት አጠቃያቂ ነው። ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በፌዴሬሽን ምክርቤት ውክልና ቢኖራቸውም እኩል ሕግ የማውጣት ስልጣን በሌለበት ሁኔታ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የፌደራል መንግስት በሚያወጣውን ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ በማሳረፊ የጋራ ማስተዳደር መርህን ለመተግበር ብሎም የተመጣጣኝ ውክልና የማግኘት መብቱ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል።

### 3.2. የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ሊከተሏቸው ይገባል ከተባሉት አማራጭ ንድፎች አንፃር

በጥናቱ በመጀመሪያው ክፍል ከቀረቡት የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች ያሉባቸው አገራት ሊኖሯቸው ስለሚገባው የሕገ-መንግስት ንድፍ አንፃር የኢትዮጵያ ንድፍ በደፈናው ወይም በጠቅላላው ሁለቱን ንድፎች አይቀበልም ወይም ከነሱ የተለየ ነው።

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት ሆሮዊትዝ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ሊወስዱትና ሊተገብሩት የሚገባቸው፣ ብሎ ያቀረበውን የተሣሣቢነት ዴሞክራሲ ንድፍ (centripetalism) ጠቅላላ ትቶታል ወይም አልተቀበለም። የማሳሳብ ዴሞክራሲ ንድፍ (centripetalism) ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች የሚያዘው መድሐኒት የአማራጭ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት (Alternative

---

[51] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 1፣50-52፣94-100 ይመለከቷል።

[52] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 51፣ 52፣ 55፣ 96፣97፣ 98፣ 99

[53] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 55

[54] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 56 እና 72

[55] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 61

[56] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 61

Vote) ነው። ኢትዮጵያ የመረጠችው የምርጫ ሥርዓት ደግሞ በብዙሃን የምርጫ ስርዓት (Majority or Plurality electoral system) ውስጥ የሚመደበውን አብላጫ ድምፅ የምርጫ ሥርዓት (First Past the Post) ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የቀረጹ ሰዎች በብሄር/ ቋንቋ ላይ ተመርኩዞ የሚነሳ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ያለባቸው አገራት ሊኖራቸው ይገባል ብሎ ያቀረበውን የሆሮዊትዝ ንድፍ አልተቀበሉትም።

የኢትዮጵያን ሕገ-መንግስት የቀረጹ ሰዎች በተወሰነም ደረጃ ቢሆን በንዱፉ ውስጥ ለማካተት ሙከራ ያደረጉት የላይፓርትን የስምምነት/ስልጣን የማጋራት ንድፍ (consociationalism) ነው። ይሁንና አንኳር የተባለውን የስምምነት/ስልጣን የማጋራት ንድፍ (consociationalism) ስለማያካትት የኢትዮጵያ ንድፍ የላይፓርት ንድፍን ከመቅረብ ይልቅ ይርቃል።

የኢትዮጵያው ንድፍ ከላይፓርት የስምምነት/ስልጣን የማጋራት ንድፍ (consociationalism) በዋነኛነት የሚጋራው በውስጥ ጉዳዮች ላይ እንደ ትምህርትና ባሕል የመሳሰሉት ላይ የመወሰን ነፃነት ክልላዊ/ አካባቢያዊ ራስን የማስተዳደር ነፃነቶች/ እና በተወሰነ ደረጃ ተመጣጣኝ ውክልና ነው። ከዚህ ውጭ አንኳር የሆኑትን የማስማማት/ ስልጣን ማጋራት ንድፍ አላካተተም። አንደኛ የምርጫ ስርዓቱ የተመጣጣኝ ውክልና (Proportional Representation) መሆን እንደሚኖርበት ላይፓርት ያመላከተ ቢሆንም የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የደነገገው የምርጫ ስርዓት የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ስርዓት (First Past the Post) ነው። ሁለተኛ የአስፈፃሚ ስልጣን መጋራትን በተመለከተ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት ምንም የደነገገው ነገር የለም[57]። ሶስት ላይፓርት ሁለት ምክርቤቶች ማዋቀር እንደ ተጨማሪ የስምምነት ዴሞክራሲ ገፅታዎች ያቀረበና የኢትዮጵያ ሕገመንግስተም ሁለት ምክርቤቶች መዋቀራቸውን ቢደነግግም የኢትዮጵያው ሁለተኛው ምክርቤት ሕግ የማውጣት ሥልጣን የለውም።

ስለዚህ የኢትዮጵያ የሕገ-መንግስት ንድፍ በአማራጭነት የቀረቡትን የላይፖርትንም ሆነ የሆሮዊትዝ ንድፎች አይቀበልም፤ አይተገብርም። በመሆኑም የሁለቱም ንድፎች አቀንቃኞች/ ደጋፊዎች በተከፋፈለ ማሕበረሰብ ሊኖር የሚገባው ንድፍ እነሱ እንደሚሉት ከሆነ ኢትዮጵያ ችግሩን ለመቅረፊ የቀረፀችው የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፊ ግማሽ እንጂ ሙሉ መልስ አይደለም። በሌላ አባባል በብሔር/ ቋንቋ ተመርኩዞ ለሚነሳ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት ሁነኛ መፍትሔው የስምምነት/ የስልጣን ማጋራት/ዴሞክራሲ (Consociationalism) ወይም የማሣሣብ ዴሞክራሲ (centripetalism) ከሆነ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስትን የቀረፁት እንዳሰቡት ለችግሩ ሁነኛ መፍትሔ አልሰጡም።

ይልቁንም የኢትዮጵያው የሕገ-መንግስት ንድፍ የአብላጫ ድምፅ ምርጫ ሥርዓት ላይ መሰረት ባደረገ የብዙሃን ዴሞክራሲ የተቃኘ ነው። ይህ ደግሞ ላይፓርትም ሆነ ሆሮዊትዝ የተከፋፈሉ ማሕበረሰቦች የምዕራባውያን አይነት ብዙሃን ዴሞክራሲ እንዳይሞክሩት ብሎም

---

[57] በተግባር በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የአስፈጻሚውን ጥንቅር በብሔር ውክልና ላይ የተመሰረተ ስብጥር እንዲሆን የተመሰረተ እንዲሆን የሚሞክር የሚታወቅ ቢሆንም ሁለት መሰረታዊ ገደቦች አሉበት። የመጀመሪያው ተመጣጣኝ አይደለም። ሌላው ፓርቲው የአራት ፓርቲዎች ግንባር እንደመሆኑ ግንባሩ ውስጥ ያልታቀፉ የብሄር/ ቋንቋ ቡድኖች መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም።

*እንዳይተገብሩ አበክረው የሚመክሩትንና የሚያስጠነቅቁትን ቸል በማለት ሳይቀይር፣ ሳይከልስ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የምዕራባውያን የብዙሃን ዴሞክራሲ ንድፍ ተቀብሏል፡፡*

## *መደምደሚያና አስተያየት*

*ላይፓርቲና ሆሮዊትዝ የምዕራባዊያን ብዙሃን ዴሞክራሲ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ተገቢ አለመሆኑን ቢስማሙም በብሄር/ቋንቋ ማንነት ላይ ተመርኩዞ ለሚነሳ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ወይም ግጭት የሚያዙት መድሐኒት ግን በመሠረታዊነት የተለያየ ነው፡፡*

*ላይፓርት የስምምነት (ሥልጣን የማጋራት) የዴሞክራሲ ንድፍ ሆሮዎትዝ በበኩሉ የማሳሳብ የዴሞክራሲ ንድፍ አማራጮች አቅርበዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ችግሩን ሊፈታ የሚችለውና የሚገባው የብሄር ሊሂቃንን ስልጣን በማጋራት ወይስ የነሱን በፖለቲካ ሚና በማሳነስ ወይም በማቀጨጭ፤ በሚለው ላይ የተለያየ አቋም ስላላቸው ነው፡፡ ላይፓርት የመጀመሪያውን ሲደግፍ ሆሮዊትዝ ሁለተኛውን ይደግፋል፡፡*

*ላይፓርት የብሄር ሊሂቃንን ሥልጣን በማጋራት ችግሩን መቅረፍ ይቻላል ብሎ ስለሚያምን ሥልጣን የማጋራት ዴሞክራሲ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ተገቢው የሕገ-መንግስት ንድፍ ነው፤ ብሎ ይከራከራል፡፡ ሆሮዊትዝ በበኩሉ ችግሩ የሚፈታው የብሄር ልሂቃንን ሥልጣን በማጋራት ሳይሆን ልሂቃኖቹ በፖለቲካ ሂደቱ ያላቸውን ወይም የሚኖራቸውን ሚና በማቀጨጭ ነው፤ ብሎ ስለሚያምን በአማራጭ ድምፅ የምርጫ ስርዓት መሰረት ያደረገ የሕገመንግስት ንድፍ ለተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ተገቢ ነው፤ ብሎ ይከራከራል፡፡*

*ሁለቱ የዘርፉ ምሁራን የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች ያሉባቸው አገራት ሊኖራቸው ይገባል፤ ብለው ከሚያቀረቡት የዴሞክራሲ ንድፍ አንፃር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት የራቀ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት የማሳሳብ ዴሞክራሲ ንድፍ* (Centripetalism) *የሚጠይቀውን የአማራጭ የምርጫ ስርዓት* (Alternative vote electoral system) *አልተቀበለውም፡፡ የአካባቢያዊ ነጻነትና ብሄር ብሄረሰብና ሕዝቦች ተመጣጣኝ ውክልና የማግኘት መብት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት እውቅና የሰጠ ቢሆንም የስልጣን መጋራት የዴሞክራሲ ንድፍ* (consociationalism) *አንኳር የሆኑትን ተመጣጣኝ የምርጫ ስርዓትና የአስፈጻሚውን ስልጣን መጋራት በግልጽ ሳያስቀምጥ አልፏቸዋል፤ ወይም ዘሏቸዋል*[58]*፡፡ በመሆኑም ከንድፈ-ሃሳብ አንጻር ሁለቱ ምሁራን የሚያቀርቧቸው ንድፎች ብቻ ከሆኑ ብሔር/ ቋንቋ ላይ ተመርኩዞ ለሚነሱ ግጭቶች መግራትና መምራት የሚያስችሉት የአገራችን የዴሞክራሲው ንድፍ ርቀት የማስኬድ ዕድሉ በጣም የሳሳ ነው፡፡*

*ከንድፍ ውጪ ከተግባር አንፃር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት ብሔር/ቋንቋ ላይ ተመርኩዞ የሚነሱ ግጭቶችን የመግራትና የመምራት ብቃቱን ለመገምገም አስቸጋሪ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት ከልደት እስከ ወጣትነቱ በተቃውሞና በድጋፍ የታጀበ ጎዞ ተጉዟል፡፡ ይህ ሕገ-መንግስት* 23 *ዓመታት አስቆጥሯል፡፡*

[58] ቂጥር 17 ይመለከቷል፤ ላይፓርት በዋነኝነት ቤልጅየምንና ደቡብ አፍሪካን እንደጥሩ ምሳሌ ያጣቅሳል፡፡ የቤልጅየም ሕገመንግስት ካቢኔው በእኩል ቁጥር ከደችና ከፈረንሳይኛ ተናጋሪዎቸ እንዲዋቀር ሲደነግግ፣ የደቡብ አፈሪካው ሕገመንግስት ከዚህ በተለየ በፓርላማ በትንሹ 5% መቀመጫ ያገኘ ፖለቲካ ፓርቲ ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ በካቢኔው ውስጥ የመሳተፍ መብት ይሰጣል፡፡ ቡድኖቹን መለየት ቀላል ከሆነ የቤልጅየም ሞዴል የተሻለ ሲሆን፣ ይህ አስቸጋሪ ከሆነ የደቡብ አፍሪካው የተሻለ አማራጭ ነው ብሎ ይከራከራል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት ደጋፊዎች እንዳሉት ሁሉ ተቃዋሚዎችም አሉት፡፡ ለዚህ አንድ ማሣያ በተቀናጀ  የተቃውሞ ፓለቲካ ያሉ ቡድኖች አሁንም መሠረታዊ በሆኑ የሕገ-መንገስት መርሆዎች ላይ ተቃውሞ ያሰማሉ፡፡ ይህ ተቃውሞ በፌደራል ስርዓቱ ብሔር-ተኮርነትና እስከ መገንጠል መብቶች እንዲሁም በምርጫ ሥርዓቱ ላይ ያተኩራል፡፡ አገራዊ ምርጫ በተካሄደም ቁጥር የምርጫ አጀንዳ ሆኖ የሚቀርበው ከሕገ-መንገስቱ መልስ ባሉ ጉዳዮች እንደ ኢኮኖሚያዊ ማሕበራዊ ሳይሆኑ ሕገ-መንግስቱ ራሱ ነው፡፡

ይህ እንደ አንድ ትልቅ ፈተና ሊወሰድ ቢገባውም አጠቃላይ በብሄር/ ቋንቋ ላይ ተመርኩዞ ለሚነሳ የፖለቲካ አለመረጋጋት ወይም ግጭት በመቀነስ ረገድ የሕገ-መንግስቱን ስኬትና ድክመት በዚህ መመዘን አስቸጋሪ ነው፡፡ በተለይ በአሁኑ ሰዓት የሕገ-መንግስቱ ስኬትና ድክመት ግምገማ እጅግ ቁልፍ የሆነው አብይ ችግር አሁንም በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ሕገ-መንግስቱን ከውልደቱ እስከ ጉርምስና ባለው ሂደት አገሪቱን ያስተዳደረ መሆኑ ነው፡፡ የዚህን ሕገ-መንግስት ስኬት ወይም ድክመት ሌላ ስልጣን ይዞ የማያውቅ ፓርቲ በምርጫ ስልጣን ላይ ወጥቶ የተከታታይ ፓርቲዎች ስልጣን መውረድና መውጣት ባልታየበት ሁኔታ ግምገማውን ማካሄድ አስቸጋሪ አድርጐታል፡፡

ሌላኛው ግምገማውን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ቁልፍ ችግሮች ውስጥ በንድፈ-ሃሳብና በተግባር መካከል ያለው ልዩነት ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ላይ ከሚቀርቡ አብይ ትችቶች አንዱ ሕገ-መንግስቱን በተግባር ላይ አያውለውም፤ የሚለው ክስ ነው፡፡ ከተቃዋሚዎች ጀምሮ ሥርዓቱን ያጠኑ ምሁራን ሕገ-መንግስቱን በተግባር የመተርጐም ችግርን በአጭር ቃል ለመግለጽ በቅርጽ ፌደራላዊ በተግባር አሀዳዊ ብለው የሰላ ትችት ይሰነዝራሉ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ ሁኔታ አዲሱን የብሔር-ተኮር የፌደራል ፖለቲካ ሥርዓት ሙከራ ስኬትና ድክመት በተለያዩ ምክንያቶች መገምገም አስቸጋሪ ነው፡፡ በተከፋፈሉ ማህበረሰቦች የሕገ-መንግስት ንድፍ ምን አይነት መሆን አለበት፤ የሚለውን የዘርፉ ምሁራኑ ከቀመሩት ንድፍ አንጻር ከታየ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት በብሄር/ ቋንቋ ማንነት ላይ ተመረኩዘው ለሚነሱ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ አላበጀም፡፡ እንዲያውም የንድፉ ይዘት የተከፋፈሉ ማህበረሰቦች እንዳይከተሏቸውና እንዳይተገብሯቸው የመከሩትን ችላ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም መሰረታዊው ጥያቄ እንዴት የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ስርዓት መሰረት ላይ ያደረገ የብዙሃን ዴሞክራሲ ስርዓት ይዞ ቀጠለ? የሚለው ነው፡፡ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የሕገ-መንግስት ማዕቀፍ ስኬታማ ነው፤ የሚባል ከሆነ ለስኬቱ ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ሕገ-መንግስቱን የቀረጹ ሰዎች ንድፍ እንደ ሌላ አማራጭ ሊወሰድ ይችላልን? ወይስ ሕገ-መግስቱ በአካባቢያዊ  የአስተዳደር ነፃነት ላይ ትኩረት መስጠቱ ላይፖርትና ሆሮዊትዝ ትኩረት ያደረጉባቸው የማእከላዊ መንግስትና የምርጫ ሥርዓቱ አደረጃጀትና አወቃቀር እዚህ ግባ የሚባል ፋይዳ የላቸውም ማለት ነው? ወይስ በኢትዮጵያ ሁኔታ አሁን ያለውን ንድፍ ስኬታማ የሚያደርጉ ሌሎች ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊ ምክንያቶች አሉ? ካሉስ ምንድን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ያስነሳል፡፡

እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የሕገ-መንግስቱን በብሄር/ ቋንቋ ልዩነትና ማንነት ላይ ተመርኩዞ ለሚነሳ  ግጭት ያስቀመጠውን ስትራቴጂ ስኬትንም ሆነ ድክምት ለማወቅ፣ ለመመዘንና ለመገምገም የበለጠ ከባድና ውስብስብ ያደርጉታል፡፡ እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎችም ተጨማሪ ምርምር የሚጠይቁ ናቸው፡፡